ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞክራሲያ ቅጽ 35 ቁጥር 4 የካቲት 2002 ዓ.ም.

## የካቲት 66-- የሕዝባዊ አመፅ መንፈስ ያብባል

*የየካቲት 66 ታሪካዊ አብዮት ከፈነዳ 36 ዓመት አለፈ። ይህ ሕዝባዊ አብዮት የአመፅ ክስተት ፀራቸው ለሆነው ሁሉ መርዶ ነግሮ ለጥቂቶች ጥቅምና ድሎት ብቻ የቆመውን ኋላ ቀር የአፄውን ሥርዓት ያንኮታኮተ ነበር። ግብታዊ ነው ቢባልም ለዓመታት ተካሂደው በነበሩና የደም ግብር በተከፈለባቸው የአርሶ አደር አመፆች፥ የላባደር አድማዎች፥ የተማሪና ምሁራን ትግሎች ተኮትኩቶ ያደገ፣ ያበበ ነበር። የሕዝብ አመፅ መቸ እንደሚፈነዳ በቀን ደረጃ ማወቅ ቢገድም የአፄው ሥርዓት ግን ወደ መቀበሪያው መድረሱን ያወቁ ምሁራን የፖለቲካ ድርጅትን መመሥረት ማስፈለጉን ተረድተው በሚያዝያ 1964 ኢሕአፓን መሥርተው ነበር።*

*የየካቲት አብዮት የትግል መንፈስ በሀገራችን ታሪክ ከፍተኛ ቦታን ይዞ የተገኘበት ምክንያቶች አያሌ ሲሆኑ ዛሬ ሀገራችን በአጥፊ ዘረኛ ቡድን መዳፍ ስር ገብታ ስትሰቃይ መታወስና መታደስ ያለበት ሆኖ ይገኛል። ለሥዩመ መለኮቱ ንጉሥ ሰግዶ፣ ድህ ድሮስ ምን አውቆ ከመገዛት በቀር ይባል የነበር ሕዝብ፣ በማንነቱ የተነሳ ይናቅ ይበደል የነበረ ሕዝብ፣ የጭቆና ጭጋግን ከአንጎሉ ገፍፎ፣ የአመፅ ደወልን አሰምቶ፣ የእምቢኝንም ከበሮ ጎስሞ፣ አልገዛም እኔ ከእንግዲህ በኋላ ብሎ በጋራ ሲነሳ ማንም ኃይል ሊያቆመው አልቻለም። ጨቋኙ ሥርዓት የመጀመሪያውን የሕዝብ ተቃውሞ ሲያይ ሽበረክ ብሎና ርዶ አልወደቀም። ሕዝባዊ እንቅስቃሴውን ለማፈን የጦር ኃይሉንና ፖሊሱን አሰማርቶ ደም አፍሷል። ሕዝብ ግን ቢበዛ ድንጋይ አሊያም ሰለማዊ ሰልፍን መሳሪያው አድርጎ ለግቡ ተዋድቋል። ሥርዓቱ ይመካበት የነበረው ጦርም ቀስ በቀስ ሊናድና ለአፄው መታዘዙን ሊያበቃም የቻለው ከመስዋዕትነት በኋላ መሆኑም የሚታወስ ነው። የሕዝባዊ መነሳሳቱ ምንም እንኳን በከተሞች ያተኮረ ቢሆንም ለትግል ቆርጦ የተነሳው ሕዝብ በግድያ ሳይሸማቀቅ ቀጣይ ትግልን በማካሄድ፣ ሥርዓቱ ትግሉን ሊያደናቅፍና ሊሸነግል ሲጥር በጠቅላላ የሠራተኛ አድማ ትግሉን በማፋፋም የሥርዓቱን ውድቀት ሊያመጣ ችሏል። የሕዝብ ድል በምርጥ መኮንኖች ቢቀማም የየካቲት አብዮት ኋላ ቀሩን ሥርዓት በመደምሰስ ደረጃ ታሪካዊ ድልን ተቀዳጅቷል።*

*የየካቲት አብዮት ማጠየቂያው አንዳንዶች በስህተት እንደሚሉት "በባዕድ ርዕዮት የተቃኙ ወጣቶች ሊበጠብጡ በመነሳታቸው" ሳይሆን ሥርዓቱ አድኃሪና ፀረ-ሕዝብ በመሆኑ በፈለፈላቸው የማይታረቁ ቅራኔዎች ምክንያት ነው። በአገዛዙና በሕዝብ መሀል የነበረው ፈርጀ ብዙ ቅራኔ ከቶም የማይታረቅ ሆኖ በመብሰሉ ሕዝብም እንደቀድሞው ሰጥ ለጥ ብሎ ለመገዛት አሻፈረኝ በማለቱ አብዮቱ ሊፈነዳ ችሏል። በወቅታዊነት የቤንዚን ዋጋ መጨመርና የትምህርት ይዞታን ለማሻሻል ተብሎ የታቀደው ፖሊሲ (ሴክተር ሬቪው) በአስተማሪዎችና ተማሪዎች ዘንድ ድጋፍ ማጣቱ ምክንያቶች ቢባሉም ሲያመረቅዝ የቆየው መሠረታዊ ቅራኔ ለፍንዳታው ዋና ምክንያት ነበር። ይህን ዓይነቱ የቀውስ ወቅት ሲከሰት--ገዢዎች ባለፈው መንገድ መግዛት ሲያቅታቸውና ሕዝብም እንዳለፈው አልገዛም ሲል--ለውጥን ሊወልድ የሚችል ሁኔታ መከሰቱ ሁሌም ያለ ነው። ይህን መርቶ ከግብ የሚያደርስ ሕዝባዊ ድርጅት መኖር አለመኖሩ ደግሞ ለሕዝብ የሚበጅ ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን የሚወስን ይሆናል። በየካቲት 66 ኢሕአፓ የመሪነትን ሚና ለመጨበጥ ድርጅታዊ አቅም ስላነሰው የተደራጀው የወታደር ክፍል በመኮንኖች አማካይነት ሥልጣን ያዘ፤ የሕዝብን ትግል ፍሬ ቀማ።*

*መሠረታዊ ቅራኔ ስንልም በሥርዓቱና በሕዝብ መሀል የነበሩትን ፖለቲካዊና ኤኮኖሚያዊ የማይታረቁ ቅራኔዎች ማለታችን መሆኑ ግልፅ ሊሆን ይገባዋል። ከነገር ማን ይቅደም? የደም! ነውናም ሕዝብን ፍዳ ያበላና ያሰቃየው፤ ደም ያፈሰሰው ሥርዓት መወገዱን ሕዝብ በጣም ፈልጎ ነበር። ዛሬ ታሪክም የማያውቁ ክፍሎች ወይም የዚያ ሥርዓት ተጠቃሚ የነበሩና ናፋቂ የሆኑት የአፄውን ሥርዓት አቆንጅተው ሊያቀርቡ ቢፈልጉም መቸም ቢሆን መች የማይካደው ሐቅ ግን ያ ሥርዓት ለብዙኀኑ መርገም ሆኖ መቆየቱን ነው። አርሶ አደሩ በጢሰኝነትና በገባርነት ሲበዘበዝ፤ ሠራተኛው ሕዘብም መብት አልባ ሆኖ፤ የሀገር ሉዓላዊነት ተደፍሮ (የባዕድ ጦር ሰፈር በሀገሪቷ መሬት ነበረና)፤ ጥቂቶች በብዙኀኑ ላይ ሲቀልዱ እንደነበር የሚታወስ ነው። ለአፄውና ቤተሰባቸው፤ ለልዑሎችና ራሶች፤ ለሚኒስቴሮችና አቀባባይ ከበርቴዎች የተመቸችው የዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ ለብዙኀኑ ሲዖል ነበረችና ድህው ሕዝብ በላቡ ያስተማረው ወጣትና የነቃ ክፍል ለፍትህ መጮህና ጭፍን ብዝበዛን መቃወም የግድ ሆነበት። ርዕዮት፥ ወዘተ... ከዚያ ሁሉ በኋላ የመጣ ነው። ሹም ለሹም ይጎራረሳል፤ ደሀ ለድሀ ይለቃቀሳል የሚለው ብሂል ያብቃ፤ ሕዝብ መጫወቻ አይደለም ብሎ መነሳት የተገደደው ወጣት ክፍል ተነስ የሚል የባዕድ ቀስቃሽ የሚፈልግም አልነበር።*

*በባላባታዊው ሥርዓት ደይን ውስጥ ብሩህ ሕዝባዊ ቀን ታይቷቸው የለውጥ እሳትን መሬት ለአራሹ ብለው የለኮሱት ታሪክ የማይረሳቸው ባለውለታዎች የጀግኖች ሰማዕት አኩሪ ወራሾች ነበሩ። የተሻለ ሥርዓት ምኞታቸው ከሽፎ የቀረው የጥቁር አንበሳ አርበኞች፥ የነበላይ ዘለቀ፥ ለውጥን የሞከሩና መፈንቅላቸው ከሽፎ የሞት ፅዋን የተቀበሉት ሀገር ወዳዶች፤ ለሀገር የተዋደቁት ብዙ ሺህዎች*

*መንፈስና ፍላጎት ሁሉ በወጣቶቹ ሰርፆ የራስን ጥቅም ጥሎ የሕዝብን የጋራ ጥቅም ማስቀደሙ ያሸነፈበት ሁኔታ ተከስቷል። የጨቋኙ ሥርዓት ጋሻ ጃግሬዎች ያኔም ሆነ ዛሬ መሬት ለአራሹ መባሉና ብዙኀኑ አርሶ አደር ከገባርነትና ከጢሰኝነት ተላቆ ሰብዕናውንና መሬቱን፥ ምርቱን በባለቤትነት እንዲይዝ የተደረገው ትግል ይሰቀጥጣቸዋል። የብዝበዛና ጭቆና ሥርዓታቸው ግብዓተ መሬት ደወል ያቃጨለበት ነውና--መሬት ለአራሹ! ፊላጭ ቆራጭነት ያብቃ! የተባለውም ሕዝብን ሙሉ መብት ለማጎናፀፍ የተቃኘ በመሆኑ ሥልጣን በጥቂቶች ተይዞ ይቆይ ባዮችን ትላንትም ዛሬም እንዳበገነ ያለ አቅዋምና መፈክር ነው። ምንም እንኳን አፄው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሞግዚት የሚያሻው ህፃን ልጅ ዓይነት ነው ብለው ቢመፃደቁም የሀገራችን ሕዝብ ራሱን ማስተዳደር ይችላል የሚለው ፅኑ እምነት ከፊላጭ ቆራጭ አዳናቂዎች ጋር--ትላንትም፥ ዛሬም--መጋጨቱና መቃረኑ አልቀረም። የአፄው ሥርዓት እንዲሻሻል የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ በመክሸፋቸው ሥርዓቱ መወገድ አለበት የሚለው ድምጻሜ ከተራማጆቹ አልፎ የሕዝብ በመሆኑ የየካቲት አብዮት በአጭር ሊቀጭ አልቻለም። እንቅስቃሴው መሠረታዊ ጥያቄዎችን አንግቦ የተነሳ በመሆኑ የአፄው ሥልጣን መለኮታዊ ነው ከቶም የማይጠየቅ የሚለውን ማገጃ ጥሶ፤ ይጠየቃል እንጂ ምነው አይጠየቅ፤ አልፎም ይወገራል እንጂ ምነው አይወገር ብሎ ሥርዓቱን ተጋተረው--አቸነፈውም።*

*መሬት ለአራሹ ብዙኀኑን የሚመለከት መሠረታዊና ዋና ጥያቄ ሆኖ ሳለ --ዛሬም ምላሽ ስላላገኘና እንዲያውም የሀገር መሬት ለባዕዳን እየተሸጠ በመሆኑ ዋና የትግል መፈክር ነው--የእኩልነት ጥያቄም ብዙኀኑን የሚመለከት ነበር። በመሆኑም ችግሩ መነሳቱና መፍትሄንም መሻቱ የሚጠበቅ ነበር ማለት ይቻላል። ሁሉን የሚያሳይ መስተዋት ሳይሆን መሰበንት ነው ተብሏልና ጊዜ በማለፉ የአፄው ሥርዓት አስከፊነት ተዘንግቶ በሕዝብ መሀል በብሔረሰብና ሃይማኖት መሰረት ዓይን ያወጣ ልዩነት ይደረግ እንደነበርም መካድ ተጧጡፏል። ሕዝብን በአንድነት አነሳስቶ ለውጥን ለማምጣት የፈለጉ ክፍሎች ለነበረው ልዩነትና የዕኩልነት መጥፋት ምላሽ ለመስጠት መሞከራቸው ችግሩን እንዳስነሳ አድርገውና አስመስለው በማቅረብ ነጋ ጠባ ታሪክንና ሐቅን የሚሽሩ በርከት ማለታቸውም የሚታይ ነው። ያበጠው ይፈንዳ ብለው ይህች ኢትዮጵያ ለጥቂቶች ገነት ለበዙኀኑ ደግሞ እስር ቤት ናት ሊሉ የደፈሩትን ዋና ጥፋተኛ አድርገው ሊፈርጁም ተነስተዋል። የካቲትም የወለደው የትግል አቅጣጫና እምነት ሕዝብን አስተባብሮ በአንድ በማታገሉ ትክክለኛነቱን የገለጠ በመሆኑ ራሱን በዚህም ተከላክሎ ትክክለኛነቱንም አሳይቷል ብንል ስህተት አይሆንም። በየካቲት ተራማጅ ኃይሉና ሕዝብ በጋራ ነው የተነሳው--በብሔረሰብና በሃይማኖት ደረጃ አልተያየምም ነበር። ኢትዮጵያውያን እስላሞች ባደረጉት ሰላማዊ ሰልፍ ክርስቲያኖችም ተካፍለውበታል። ተማሪዎች በብሔረሰብ ሳይለያዩ፤ ላባደሮች በብሔረሰብ ሳይለያዩ በጋራ አቅዋም ወስደው በጋራ ታግለዋል። ይህ ሁሉ ስለዕኩልነትና አብሮ መኖር፤ ሰለ ትምክህት ጎጂነት፤ ኢትዮጵያን በእኩልነትና በዴሞክራሲ በአዲስ ለመገንባት መታገል አስፈላጊነት፤...ወዘተ የተደረገው ቅስቀሳ ውጤት ነው። ይህን የየካቲት*

*መንፈስ ለማጫጫት ግን ጠባቦችም ሥርዓቱም መወራጨታቸው ደግሞ የታየ ሐቅ መሆኑ ሊረሳ አይገባም፡፡*

*ትላንትም ዛሬም ሊድበሰበስና ሊካድ ወደሚፈለገው ሐቅ መለስ ስንል ደግሞ ችግሩን የቀፈቀፈው የነበረው ሥርዓት መሆኑን መካድ መቼም አንችልም፡፡ ሐሰተኛ ያወራውን ፈረሰኛ አይመልሰውም ሆኖ የተደጋገሙ ሀሰቶች እውነት ሊመስሉ እየዳዳቸው የተወሰኑ ክፍሎችን ቢያደናግሩም ዕኩልነትን በተመለከተ ችግሩ ከነበረው ሥርዓት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንዳንዶች ሐቅን በአፍጢሙ ደፍተው ለምሳሌ የኤርትራን ችግር ኢሕአፓ ፈጠረው ወይም ለሻዕቢያ ድል ኢሕአፓ በወታደሩ ውስጥ ያካሄደው ሻጥርና ቅስቀሳ ጠቀመው ቢሉም ሰማይ ከምድር ቢገናኝ ሊሻር የማይችለው ሐቅ ግን የኤርትራን ችግር የፈጠረውና ያባባሰው የአፄው ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡ የኤርትራ የአንድነት ኃይሎችን በመበደልና ባንዶችን በማቀፍ፣ የፌዴሬሽኑን ይዞታ ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በማፍረስ፣ ለችግሩ ወታደራዊ መፍትሄ በመሻት (የኦም ሀጀር፥ ከረን ፍጅትን ይጠቅሷል)፣ ...ወዘተ የአፄው መንግሥት የኤርትራን ችግር አጠዘው፣ አባባሰው፡፡ ቀጥሎ የመጣው አረመኔ የደርግ አገዛዝም ፖለቲካዊ መፍትሄን በመሻት ፈንታ አማን አንዶምንም ሆነ ይህንን አማራጭ በመግደል ሁኔታውን አባብሶ ለጣልቃ ገቦች በሩን ከፈተላቸውና ውድቀቱን አስከተለ፡፡ የደረግ ሠራዊት ሽንፈት የኢሕአፓሥራ ሳይሆን የመንግሥቱ ኃይለ ማርያም ኃላፊነት መሆኑ (የፈጃቸውን መኮንኖች ያስቧል) የሚካድ ሊሆን አይችልም፡፡ ኢሕአፓ ይህ ችግር በሰላምና በዴሞክራሲያዊ መንገድ ይፈታ ብሎ ቢወተውት በኃይላቸው የተመኩና ያበጡ ክፍሎች ጆሮ ዳባ ልበስ ማለታቸው ደግሞ የሚታወቅ ነው፡፡ ለማንኛውም ግን አገዛዙ በፈጠረው ቀውስና የተወሳሰበ ሁኔታ የኤርትራ ነፃ አውጪ ግንባር (ጀብሀ) የተባለው ተቋቁሞ ውጊያ ከጀመረ ከአራት ዓመት በኋላ ኢሕአፓ መመሥረቱንና ጨቅላ ድርጅት መሆኑን ማስታወስም የግድ ይሆናል፡፡ ለዚህም ነው በኤርትራ ጉዳይ ኢሕአፓን ለመውቀጥ መነሳቱ አንድም አህያውን ፈርቶ ዳውላውን ሌላም አባ በበሉ እማሆይ ተቀጡ የሚሆነው፡፡*

*በመሆኑም የሕዝብ እኩልነት ችግር ይህን ችግር ሊፈቱ በሞከሩት የመፍትሄ ሀሳብ የተቀሰቀሰ ሳይሆን በሥርዓቱ በደለኛነት የነበረና የቆየ ነው፡፡ በብሄረሰቦች መሀል ልዩነት ይደረግ ነበር፣ የሃይማኖት እኩልነት አልተረጋገጠም ነበር፡፡ ይህ ጭቆና በተለይ በደቡብ ከመሬት ይዞታ ማለትም ከጪሰኝነት ጋር የተያያዘ ነበርናም ችግሩ በቀላሉ ሊታይ የሚችል አልነበረም፡፡ የሕዝብ እኩልነት ይረጋገጥ፣ ራሰ በራስ ማስተዳደር እውን ይሁን ያሉትም ሥርዓቱ ለፈጠረው ከፋፋይና ሀገር ጎጂ ሁኔታ መፍትሄ ፈለጉ እንጂ ያልነበረን ሁኔታ አልፈጠሩም፡፡ ለዚህም ነው የካቲት ስንል የሕዝብ እኩልነትን የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ የተካሄደ ትግል መሆኑን የምንረዳው፡፡ የሀገርና የሕዝብ አንድነትም በአስተማማኝ ዴሞክራሲያዊ መሠረት ላይ ሊከሰት የቻለ ባለመሆኑ-- ጭቆና ስለነበር-- ይህን  ችግር ማስወገድ የግድ አስፈላጊና ለትግሉም ስኬት ወሳኝ ነበር፡፡ ሀገር*

ሰላም ነው፤ ሕዝብ አንድ ነው፤ የተበደለ የተጨቆነ የለም ብሎ ራስን እንደ ሰጎን በአሸዋ ቀብሮ በምኞት ሰረገላ መጋለቡ ቢቻልም ለሀገር የሚበጅ ባለመሆኑ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነት የሚሹ ይህን አንድነት የሚፃረረውን ሁሉ ጋሬጣ ለማንሳት፥ ለማስወገድ መጣር ግዴታቸው ነበር:: የአፄው ኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ዜጎች ብሎ የመደበ ነበርና ይህ ያስከተለውን በደል መካዱ ወደፊት የሚያራምድ አልነበረም:: ጭቆናና በደል ባልነበር፤ ተበደልን፥ መብት ተነፈግን የሚል ሕዝብ ባልነበር ማን ቢሆን ማን የብሔረሰብ ጥያቄ ቢል ሰሚ ባላገኘም ነበር:: በየካቲት በአንድነት የተነሳውን ሕዝብ በማጥቃት፤ ሕብረ ብሔር ድርጅቶችን በማሳደድና በሽብር በመምተር ለጠባቦች ምቹ መንገድ አገዛዞቹ በተለይም የመንግሥቱው አረመኔ ስብስብ ባይከፍትላቸው ኖሮ ወያኔ ባላመቸው ነበር:: ኢትዮጵያዊነትን ዶጋ አመድ በማግባቱ የማይናቅ ሚናን የተጫወተው ሐራሬ በፈረጠጠው ኮለኔል የሚመራው አገዛዝ እንደነበር መካድ የሚቻል አይደለም::

የየካቲት አብዮት ያለፈውን የገረጀፈ ሥርዓት ቀብሮታልና ወደዚያ ለመመለስ የሚከጅሉት ሁሉ በከንቱ መሆኑን በጊዜ ማመን ይኖርባቸዋል:: የታሪክ ሚና የኋላ ማርሽ የለውም:: ያልነበረን ወርቅ ጊዜ ነበረ ብሎ መመኘቱ ቅዠትና ብስጭት እንጂ ክስተት ሆኖ አለ የሚል አይደለም:: የካቲት የሰጠን መልዕክት ያለፈው ደቋል፤ ለመጪውና ለአዲሱ ተዋደቁ የሚል ነው:: የካቲት የሰጠን መልዕክት የተባባረ ሕዝብ ታሪክን ይገራል፤ የሚመኘውንም ማግኘት ይችላል ተባብሮና ቆርጦ ከታገለ የሚል ነው:: ሥልጣን የያዙት ምንኛ በኃይላቸው ቢኩራሩ ሕዝብ በጋራ ከተነሳ ያቸንፋቸዋል የሚል ነው የየካቲት መመሪያ:: ሕዝብም በርካታ የትግል መሳሪያዎችና መንገዶች እንዳሉትም የካቲት 66 ጠቁሟል:: ከአገዛዙ ፍቃድ ውጪ ሰላማዊ ሰልፎችን ማካሄድ፤ ጠቅላላ የሥራ ማቆም አደማ ማድረግ ወዘተ... ሁሉም ውጤታማ ሆነው ታይተዋል:: ዛሬ ሕዝባዊ አመጽ ስንልም ጠቃሚ የሚሆን ትምህርት ተገብይቷል:: የኅብረተ ሰቡ ክፍሎች (ተማሪ አስተማሪው፥ ላባደሩ ታክሲ ነጂው፥ ሴቱ ወንዱ፥ ሴትኛ አዳሪው ቄሱ፥ ቢሮ ሠራተኛው ወታደሩ ፖሊሱ) ሁሉም ከተባበሩ ክንዳቸው ፈርጣማና ጠላትን የሚያደቅ መሆኑም ታይቷል:: ከዚህ ሌላ የየካቲት አብዮት ግልፅ አድርጎ ያለፈው ሀቅ ደግሞ ትግልና ድል ሁሌም መስዋዕትነትን ጠያቂ መሆናቸውን ነው:: ዛሬ ለተቀማጭ ቅርቡ ሆኖ ሳይደሙ ቀርቶ ሳይታገሉ ድልን እንቀዳጃለን ባይ የምላስ ፋኖዎች በዝተው ባለበት ለትግል መሰዋት ከስህተት ተመድቦ የታገለው በከንቱ እንዳለቀ፤ ያታገለው ደግሞ እንዳስጨረሰ የሚወነጀልበት ሁኔታ ብቅ ብሏል:: ሰባት ዓመት እንዳይማሩ ሰባ ዓመት ይደነቁሩ ነው ነገሩ:: ታሪካችንን ብንቃኝ ኢትዮጵያ ተከብራ የቆየችው ብዙ ደም ፈሶ፤ ከባድ መስዋዕትነት ተከፍሎ እንጂ በምለላና ልመና አይደለም:: ትግል ከተባለ መስዋዕትነት አለ:: ከመሞት መበርከት፤ የመጣውን ቆሻሻ ሁሉ በትዕግሥት መሸከም የሚሉ ከበዙ ሀገር ትዋረዳለች፤ ጭቆናም አይወገድም:: ጠላት ጉልበት አለው በሚል መራድ ከሰፈነም ሀገር አድን ትግል ሊካሄድ አይችልም:: ዛሬ የወያኔና ደጋፊዎችን ጉልበት አይተው የሚርዱ፤ ለትግልና ለሀገር መሰዋት በከንቱ ማለቅ ነው ብለው የሚደመድሙ ሀገር አድን ትግል ለማካሄድም ሆነ በዚህ ትግል ሊሳተፉ የሚችሉ አይደሉም:: ጥይት

ሳይተኮስ ብረት አውርደዋል፤ ትጥቅ ፈተዋል፤ ፍረሃትን ማሸነፍ አቅቷቸው እጅ ሰጥተዋል። ከዚህ አቅዋም ወደ ዘመናዊ ባንዳነትና ተለጣፊነት ሽርተት ማለቱ ብዙ ጉዞን የሚጠይቅም አይሆንም። ኢሕአፓ በየካቲትም ሆነ ፋሺስታዊ መኮንኖች ሥልጣንን ከጨበጡ በኋላ ታግሎ መስዋዕትነትን ከፍሏል። በሽብር ሕዝብን የፈጀ የኮለኔሉ አገዛዝ እንጂ ኢሕአፓ አልነበረም። ኢሕአፓ "ሕዝብን አላስጨረሰም" አታገለ እንጂ--ሕዝብን የጨረሰ የመንግሥቱ አገዛዝ ነው። የአንዱን አበሳ በሌላው ላይ ማበስ የማይገባ ከመሆኑ ሌላ ወንጀልም ሊባል የሚችል መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

የማንኛውም ሀገር ዜጋ ግዳጅ አለውና ከዚሁም መጀመሪያው ሀገሩን መጠበቅ፤ መንከባከብ ነው። ሚሊዮኖች ሀገራቸውን ጥለው ሊሸሹ ሊሰደዱ አይጠበቅም፤ ሊሆን የሚችልም አይደለም። ሰው ሲሰደድ ከማንነቱና ከህሊናውም ጋር ነውና ከሀገር ወጣሁ ብሎ ሀገርን መርሳት ከክህደት የሚፈረጅ ጥፋት ነው። ከራስ በላይ ነፋስ የሚሉ በዝተው በነበረ የየካቲት አብዮት ተካሂዶ ጨቋኙ ሥርዓት ባልተወገደ ነበር። ሀገርንም ለማዳን ሕይወቴ ለሀገሬ የሚል ዜጋ መበርከቱን፥ መብዛቱን የግድ ይላል። የጭቆናው ክፋትና መራራነት የጋገረውና ያፈዘዘው ከበዛ ሀገር ወዮላት ማለት እንችላለን። ዜጎች ሁኔታው ደይኖና ከፍቶ ባለበት አንጀታም ሆነው በመራራው ትግል ሊሰማሩ የሚችሉት ቀቢፀ ተስፋን አስወግደው፤ ፍርሃትን ገርተውና በቁጥጥር አስገብተው፤ ግለኝነትን አሽቀንጥረው ጥለው እምቢኝ ለሀገሬ ብለውና ሞት አይፈሬ ሆነው ሲነሱ ነው። የየካቲትና የዚያን ጀግና ትውልድ አርዓያነት ሲቀበሉ ነው።

ባለጌ ሞት ቢያፈጥ ማንስ ሊፈራ ነው፤
የእኛ ተልዕኮ እኮ ኢትዮጵያን ማዳን ነው
የሚሉ ቆራጦች ያስፈልጋሉ ማለት ነው። ይህን ነው የካቲት ያስተማረን። ድልንም ለማስከበር፤ ላለመነጠቅ ተደራጅቶ መገኘት ወሳኝ መሆኑን የካቲት አሳይቷል። ሕዝብን አደራጅቶ ማታገልና መታገል ዛሬም ዋናው ተልዕኳችን ሆኖ ይገኛል።

የየካቲት የአመፅ መንፈስ ያብብ!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!